በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት፣ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT, HOUSING & CONSTRUCTION

ከ/ል/ቤ/ኮ/ሚ/ር 28፡2007
*የመጀመሪያ ዕትም*
20/12/2007

# የህዝብ እና የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የአገልግሎት፣ የአስተዳደር እና የህንፃው የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርድ

## (በፈርጅ አንድ ከተማ አስተዳደሮች የሚተገበር)

ሚያዝያ 2007 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ

*መቅድም* ...... III
*መግቢያ* ...... IV
1. ወሰን ...... 1
2. ትርጓሜ ...... 1
ክፍል አንድ፡- የህዝብ እና የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ የአገልግሎት፣ የአስተዳደር እና የህንፃው የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርድ ...... 3
**3. የአገልግሎት ስታንዳርድ ...... 3**
3.1. ጠቅላላ መሥፈርት ...... 3
3.2. የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የደንበኞች የፊትለፊት/ የቀጥታ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ...... 4
3.2.1. የሰራተኞች ቢሮ እና የእንግዳ መቀበያ ቦታ/reception/ ...... 4
3.2.2. የተገልጋዮች የመቆያ ቦታ/waiting room/ እና መስተንግዶ ስታንዳርድ ...... 4
3.3. በህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት መስጫ ቤቶች ውስጥ መሟላት ያለባቸው ቁሳቁሶች ...... 5
3.4. የጽዳትና ውበት እና የጤና አጠባበቅ ስታንዳርድ ...... 6
3.5. የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፣ ...... 6
**4. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ አስተዳደር /MANAGEMENT/ ስታንዳርድ ...... 6**
4.1. ጠቅላላ መሥፈርት ...... 6
4.2. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ባለቤትነት ...... 8
4.3. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የቁልፍ አያያዝ ...... 8
4.4. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የአገልግሎት መጠቀሚያ ታሪፍ ...... 8
4.5. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የሰው ኃይል ...... 8
4.6. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ዕቅድ ...... 9
4.7. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ክትትልና ቁጥጥር ...... 9
4.8. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የመረጃ አያያዝ ...... 9
4.9. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ...... 9
4.10. የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ...... 9
4.11. የአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች የግል ደህንነትና ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች /PERSONAL PROTECTIVE EQUIPMENT/ ...... 10
4.12. የአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ጤና አጠባባቅ ...... 10
**5. የህዝብ መፀዳጃ እና የገላ መታጠቢያ የህንፃው የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርድ ...... 10**
5.1. ጠቅላላ መሥፈርት ...... 10
**የህዝብ መፀዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ህንፃ ግንባታ ሲከናወን ከሚከተሉት ስታንዳርዶች አንፃር መፈፀም አለበት፡፡ ...... 10**
5.2. የቦታ መረጣ/SITE SELECTION/ ስታንዳርድ ...... 12
5.3. የህዝብ መፀዳጀ እና ገላ መታጠቢያ የህንጻው ዋና መግቢያ በር ስታንዳርድ ...... 13
5.4. የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሰራተኞች ቢሮ/የእንግዳ መቀበያ/RECEPTION/፣ የተገልጋይ ማረፊያ፣ የክፍሎች/CUBICLES/፣ የወንዶች የውኃ ሽንት መጠቀሚያ ቦታ አካፋይ እና የእጅ መታጠቢያ ስታንዳርድ ...... 14
5.4.1. የሰራተኞች ቢሮ፣ የእንግዳ መቀበያ/reception/ እና የተገልጋይ ማረፊያ ቦታ ...... 14
5.4.2. የህዝብ መጸዳጃ ክፍሎች/cubicles/ ስታንዳርድ ...... 14
5.4.3. በህዝብ መፀዳጃ ቤቶች የአካል ጉዳተኞች መጸዳጃ ክፍሎች/cubicles/ ስታንዳርድ ...... 15
5.4.6. የህዝብ የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ስታንዳርድ ...... 17

**ክፍል ሁለት፡-የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የአገልግሎት፣ የአስተዳደር እና የህንፃው የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርድ** ........ 19
6. **የአገልግሎት ስታንዳርድ** ........ 19
7. **የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት የአስተዳደር ስታንዳርድ** ........ 19
7.1. ጠቅላላ መሥፈርት ........ 19
7.2. የጽዳትና ውበት አጠባበቅ ስታንዳርድ ........ 21
7.3. የጽዳትና ውበት ስራዎችና የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ........ 21
7.4. የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ........ 23
8. **የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ የህንፃው የውስጥ መገልገያዎች ስታንዳርድ** ........ 23
8.1. ጠቅላላ መሥፈርት ........ 23
8.2. የቦታ መረጣ/SITE SELECTION/ ስታንዳርድ ........ 24
8.3. የህንጻው ዋና በር ስታንዳርድ ........ 26
8.4. የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የክፍሎች /CUBICLES/ እና የእጅ መታጠቢያ ስታንዳርድ ........ 26
**ዕዝሎች** ........ 29
ዕዝል አንድ፡-የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች መነሻ ዲዛይን- (SCHEMATIC DESIGN) ........ 29
ዕዝል ሁለት፡- የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ዲዛይን ........ 30
ዕዝል ሶስት፡- የጋራ መፀዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች መነሻ ዲዛይን- (SCHEMATIC DESIGN) ........ 31
**የማጣቀሻ ሰነዶች** ........ 32

## መቅድም

የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በከተሞች ለዜጎች የሚሰጠው አገልግሎት ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልፅና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት በከተሞች እንዲተገበሩ የማድረግ ሀገራዊ ተልዕኮ ወስዶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት ለማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርድ የሚያዘጋጅ የሥራ ክፍል አቋቁሙ ስታንዳርዶች እየተዘጋጁ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒ ካቢኔ እየፀደቁ በከተሞች አገልግሎት ላይ እንዲውሉና የአገልግሎት አሰጣጡም እንዲሻሻል በማድረግ የዜጎች እርካታ ከፍ እንዲልና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የበኩሉን ብርቱ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ስታንዳርዶቹም በአገሪቱ ከተሞች የሚተገበሩ በመሆናቸው የኩባንያ/Company/ ስታንዳርዶች የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ይህ የህዝብ እና የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የአገልግሎት፣ የሥራ አመራርና የህንፃው የውስጥ መገልገያዎች ስታንዳርድ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች የሥራ ቡድን /working group/ በማቋቋም የተዘጋጀ ሲሆን የቡድኑ አባላትም ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዳይዜሽንና ምዘና መምሪያ እና ከከተማ ፕላን ጽዳትና ውበት ቢሮ የተውጣጡ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ለዝግጅቱም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች/ግብዓቶች ከድረ-ገፅ፣ ከከተሞችና ከክልል ቢሮዎች መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ሠነዶችን እና በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጥ ነባራዊ ሁኔታ የሚያመለክት መረጃ (baseline data) በማሰባሰብ እና ረቂቅ ስታንዳርዱን ለባለድርሻ አካላት በማቅረብ ግብዓት በማሰባሰብ የተዘጋጀ ነው፡፡

## መግቢያ

ከተሞቻችን ፅዱ፣ ውብና ለኑሮ ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ ራዕይ በመሰነቅ ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡ እስካሁን በተደረገው ርብርብ ቀላል የማይባሉ የሚታዩ ውጤቶች ከመመዝገባቸው ባለፈ ፈጣን ለውጥ ጭምር ማምጣት ተችሏል፡፡ የተመዘበው ውጤትና የመጣው ፈጣን ለውጥ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም ብዙ ህዝብ በሚንቀሳቀስባቸው፣ በሚሰበሰብባቸውና መንገደኞች በሚበዙባቸው አካባቢዎች ለህዝቡ አገልግሎት የሚሰጡ መፀዳጃ ቤቶች ባለመገንባታቸው በተለይም አደባባዮች፣ የአውቶብስ መናኸሪያዎች፣ የታክሲ መነሻና መዳረሻ አካባቢዎች፣ የህዝብ መናፈሻ አካባቢዎች እንዲሁም የገበያ አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ ለአካባቢ ብክለት ተጋልጠው ይገኛሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከተቆረቆሩ ረዥም ዕድሜ ባስቆጠሩ ከተሞች ማዕከላዊ አካባቢዎቻቸው (inner city) የከተማን የመሬት አጠቃቀም ፕላን ያልተከተለ በመሆኑ የህዝቡ አሰፋፈር የተፋፈገና ቁጥሩም ብዙ በመሆኑ እንዲሁም ነዋሪዎቹ የግል መፀዳጃ ቤቶችን በተገቢው ሁኔታ ገንብተው እንዳይጠቀሙ አሰፋፈሩ በፈጠረው ችግር ምክንያት ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ የመኖሪያ መንደሮቹ ለአካባቢ ብክለት ከመጋለጣቸው በተጨማሪ የነዋሪውም መሠረታዊ ጥያቄ የሆነው የመፀዳጃ ቤቶችና የገላ መታጠቢያዎች ችግር እንዳልተቀረፈ ግልፅ ነው፡፡

በመሆኑም የአካባቢ ብክለት በህዝቡ ጤና ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅዕኖ፣ የህዝቡን መሠረታዊ የአገልግሎት ጥያቄና በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ ያለውን ከተሜነት ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ከተሞችን ፅዱ፣ ውብና ለኑሮ ምቹ ለማድረግ የተሰነቀውን ራዕይ ዕውን ከማድረግ አንፃር ለችግሮቹ ዘላቂ የመፍትሄ አማራጮችን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ የህዝብ እና የጋራ መፀዳጃ ቤቶችንና የገላ መታጠቢያዎችን በተገቢዉ ቦታ ላይ ገንብቶ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት፣ የአስተዳደር ሥርዓቱን ለማጠናከር እንዲሁም የከተማ ነዋሪዎችም ሆኑ መንገደኞች ሳይቸገሩ ተገቢውን ቀልጣፋ አገልግሎት በተገቢው ቦታና ጊዜ እንዲያገኙና የአካባቢ ብክለት እንዲቀንስ ለማድረግ ይህንን ስታንዳርድ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

ዓለማውም የከተሞቻችን የመኖሪያና የሥራ አካባቢዎች እንዲሁም መንገደኞች የሚበዙባቸው አካባቢዎች ከብክለት የፀዱ፣ ለሥራና ለኑሮ ምቹ እንዲሆኑ እንዲሁም የዘርፉን አገልግሎት ለሚፈልጉ ለከተማው ነዋሪና ተንቀሳቃሽ መንገደኞች የሚሰጠው አገልግሎት ስታንዳርዱን የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ የተገልጋዮች እርካታ ከፍ እንዲል ለማድረግ ነው፡፡

ስታንዳርዱ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ክፍል አንድ የህዝብ መፀዳጃ እና የገላ መታጠቢያ እንዲሁም ክፍል ሁለት የጋራ መፀዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ሆኖ በእያንዳንዱ ክፍሎች የአገልግሎት አሰጣጥ፣ የሥራ አመራር እና የመፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ህንፃ የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርዶችን አካቶ የተዘጋጀ ነው፡፡

## 1. ወሰን

ይህ ሰነድ የህዝብ እና የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የአገልግሎት፣ የስራ አመራር /Management/ እና የህንፃውን የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርዶችን ያካተተ ሲሆን ስታንዳርዱም በፌርጅ አንድ ከተማ አስተዳደሮች በቀጥታ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ወደ ሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች በሂደት እየሰፋ የሚሄድ በመሆኑ እንዲፈፅሙት አስገዳጅ ባይሆንም ከተሞቹ በራሳቸው ፍላጎት መፈጸም ይችላሉ፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ ስታንዳርድ የሚከተሉት ቃላት ቀጥሎ ካለው ትርጉም አንፃር ብቻ ይወሰዳሉ፡፡

2.1. **ተገልጋይ**፡-በህዝብ መጸዳጃ እና በገላ መታጠቢያ ቤቶች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማግኘት ባለው መብት መሰረት መገልገል የፈለገ ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው፤

2.2. **ተጠቃሚ**፡-በጋራ መጸዳጃና በገላ መታጠቢያ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማግኘት በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት የአገልግሎቱ ባለመብት ተገልጋይ ግለሰብ ነው፤

2.3. **የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ አገልግሎት፡-** የህዝብ እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው አካባቢዎች ማለትም በአውቶብስ መናኸሪያዎች፣ በታክሲ መናኸሪያዎች፣ በህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች፣ በመናፈሻዎች፣ የህዝብ በዓላት በሚከበሩባቸው ቦታዎች፣ በገበያ ስፍራዎች እና በመሳሰሉት ቦታዎች የመፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ግንባታ በማካሄድ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤

2.4. **የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት**፡-የከተማውን ፕላን ባልተከተለ አሰፋፈር በተለይም በተጨናነቁ በከተማ ማዕከላዊ አካባቢዎች (inner city) ለሚኖሩና የግል መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ለሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተገንብቶ የሚቀርብ አገልግሎት ነው፤

2.5. **የአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች፡-** በህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለተገልጋይ የሚያቀርቡ በቋሚነት፣ በኮንትራት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥረው የሚሰሩ ሰዎች ናቸው፤

2.6. **የህዝብና የጋራ መጸዳጃ እና ገላ መታጠቢያ ክፍሎች**/cubicles/፡- በህዝብና የጋራ መጸዳጃ እና ገላ መታጠቢያ ቤቶች ውስጥ ተከፋፍለው የተገነቡ የመጸዳጃ እና ገላ መታጠቢያ ክፍሎች ናቸው፤

2.7. **ፍሳሽ ቆሻሻ**፡-ከህዝብ እና ከጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች የሚመነጭ ቆሻሻ ውሃ እና ውሃ አዘል ቆሻሻ ነው፤

2.8. **ደረቅ ቆሻሻ**፡-ከህዝብ እና ከጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች የሚመነጭ ጥቅም የማይሰጥ ወይም የማያስፈልግ ተብሎ የሚጣል ጠጣርና ከፊል ጠጣር ቆሻሻ ነው፤

2.9. **የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር**/sewer system/፡-ፍሳሽ ቆሻሻን ከሚመነጭበት እስከሚወገድበት ለማስተላለፍ የሚዘረጋ የፍሳሽ ቆሻሻ ማውረጃ/ማስተላለፊያ ዝግ ማፋሰሻ ስርዓት ነው፤

2.10. **ሴፕቲክ ታንክ፡-** ማለት የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር በሌለባቸው ከተሞች ከህዝብ እና ከጋራ መጸዳጃ እና ገላ መታጠቢያ ቤት የሚመነጭ ፍሳሽ ቆሻሻን በጊዜያዊነት ለማጠራቀም የሚያገለግል ጉድጓድ ነው፤

2.11. **የጎርፍ ማስወገጃ መስመር**/drainage line/፡-በመንገድ ግራና ቀኝ ለጎርፍ መውረጃነት የሚገነባ ዝግ ወይም ክፍት ቦይ ነው፤

2.12. **ተወርዋሪ መሽንጎሪያ**፡-በህዝብ እና በጋራ መጸዳጃና በገላ መታጠቢያ ቤት ክፍል በር ላይ ከውስጥ በኩል ለመቆለፊያነት የሚያገለግል ከብረት ወይም ከሌላ ጠንካራ ቁስ የተሰራና በቀላሉ መከፈት የሚችል መዝጊያ ነው፤

2.13. **ባለሳህን/ተርኪሽ መጸዳጃ፡-** በህዝብ እና በጋራ መጸዳጃ ክፍል ውስጥ ከወለሉ ጋር ተለጣፊ የሆነ ከሴራሚክ፣ ከሲሚንቶ ወዘተ የተሰራ መጸዳጃ ነው፤

2.14. **ባለመቀመጫ መጸዳጃ፡-** በህዝብ እና በጋራ መጸዳጃ ክፍሎች ውስጥ ከመሬት ከፍ ብሎ የተገነባ እና ከሴራሚክ የተሰራ መቀመጫ ያለው መጸዳጃ ነው፤

2.15. **ነጠላ የፊት መታጠቢያ ሳህን፡-** በህዝብ እና በጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ውስጥ በአንድ ጊዜ አንድ ተገልጋይን ብቻ ማስተናገድ የሚችል የእጅ ወይም የፊት መታጠቢያ ሰሃን ማለት ነው፤

2.16. **ባለአግዳሚ የፊት መታጠቢያ ገንዳ**፡-በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ተገልጋይን ማስተናገድ የሚችል የእጅ መታጠቢያ ገንዳ ማለት ነው፤

2.17. **አገልግሎት ሰጪ፡-** የህዝብ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ቤት አገልግሎትን በዚህ ስታንዳርድ መሰረት ለተጠቃሚዎች እንዲያቀርብ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

2.18. **የወንዶች የውሃ ሽንት መጠቀሚያ ቦታ አካፋይ**/urinal/፡-በህዝብ መጸዳጃ ቤቶች ውስጥ ለወንዶች ለውሃ ሽንት መጠቀሚያነት ብቻ የሚያገለግል ነው፤

2.19. **የተጣራ የበር ስፋት**፡-የህዝብ እና የጋራ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ የክፍሎች ወይም የህንጻው በር ማቀፊያውን ሳይጨምር የሚኖረው የበር ስፋት ነው፤

2.20. **የደንበኞች የፊት ለፊት/ የቀጥታ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ**፡-የህዝብ መጸዳጃ እና ገላ መታጠቢያ አገልግሎት ሰጪው አካል ተገልጋዮችን በምን ሁኔታ ማስተናገድ እንዳለባቸው የሚደነግግ ስታንዳርድ ነው፤

2.21. **የመጠቀሚያ ታሪፍ፡-** የህዝብ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ አገልግሎቶችን ለማግኘት ተገልጋዩ የሚከፍለው የክፍያ መጠን ነው፤

2.22. **ፈርጅ አንድ ከተማ አስተዳደሮች**፡-ከሜትሮፖሊስና ከሪጂዮፖሊስ አስተዳደሮች ቀጥለው በሦስተኛ ደረጃ ከተማነት የተፈረጁ የክልል ከተሞች ናቸው፤[1]

[1] የተሻሻለው የከተሞች ልማታዊ መልካም አስተዳደር ግንባታ ማዕቀፍና የማስፈፀሚያ ሥልቶቹ ገጽ 134 (iii)፣

# ክፍል አንድ፡- የህዝብ እና የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ የአገልግሎት፣ የአስተዳደር እና የህንፃው የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርድ

## 3. የአገልግሎት ስታንዳርድ

### 3.1. ጠቅላላ መሥፈርት

ሀ) የከተማ አስተዳደሩ የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት እንዲኖር የማድረግና ንጽህናውም ሁልጊዜ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

ለ) ተቋሙ የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አዘጋጅቶ ለህዝብ አገልግሎት ሊሰጥ ከጤና ተቋም ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

ሐ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ዘወትር ቢያንስ ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 1፡00 ሰዓት አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል፤

መ) በአውቶቡስ መናኸሪያ አካባቢ ለሚዘጋጁ የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ዘወትር ቢያንስ ከንጋቱ 11፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 01፡00 ሰዓት አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል፤

ሠ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች አገልግሎት የሚሰጡበት ሰዓት በግልፅና ተነባቢ በሆነ ጽሁፍ በሚታይ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት፤

ረ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ሰጪው አካል በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎቶችን ማቅረብ አለበት፣

ሰ) አንድ ተገልጋይ ቀድሞ የመጣ ቀድሞ ይገለገላል በሚለው መርህ/principle/ መሠረት በወረፉ መገልገል አለበት፤

ሸ) አንድ ተገልጋይ በህዝብ የገላ መታጠቢያ ክፍል ውስጥ ከ30 ደቂቃ በላይ መቆየት የለበትም፤

ቀ) በህዝብ መጸዳጃ እና በገላ መታጠቢያ ህንጻዎች ፊት ለፊት የአቅጣጫ ጠቋሚ እና የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች መሆናቸውን የሚገልፅ ምልክት ሊደረግላቸው ይገባል፤

በ) በህዝብ መጸዳጃ እና በገላ መታጠቢያ ክፍሎች/cubicles/ መግቢያ በር ላይ የወንድ፣ የሴት፣ የአካል ጉዳተኛ መገልገያ መሆናቸውን የሚገልጽ ግልጽና ተነባቢ የሆኑ የጽሁፍና የምስል ምልክቶች መለጠፍ አለባቸው፤

## 3.2. የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የደንበኞች የፊትለፊት/ የቀጥታ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ/front line service delivery standard/

የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች የሚከተሉትን ማሟላት/ መተግበር ይኖርባቸዋል፡-

ሀ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች በስራ ወቅት ማንነታቸውን የሚገልጽ የስም መለያ ባጅ በማድረግ ጽዳቱን በጠበቀ አኳኋን ለአገልግሎት ሰጪዎች የሚዘጋጀውን የደንብ ልብስ መልበስ ይኖርባቸዋል፤

ለ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ለተገልጋዮች በቀናነትና ግብረገብ በተሞላበት ሁኔታ ተገልጋዮችን ማስተናገድ ይኖርባቸዋል፤

### 3.2.1. የሰራተኞች ቢሮ እና የእንግዳ መቀበያ ቦታ/reception/

የሰራተኞች ቢሮ እና የእንግዳ መቀበያ ቦታ ቢያንስ የሚከተሉትን ቁሳቁሶች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) ቢያንስ 2 ሰራተኞችን ሊያስተናግድ የሚችል ጠረጴዛና ወንበር፣

ለ) የመጸዳጃ ወረቀት፣ ሳሙና የመሳሰሉትን ቁሳቁሶች ማስቀመጫ የሚሆን መደርደሪያ፣

ሐ) የተገልጋዮች ዕቃ ማስቀመጫ መደርደሪያ፣

### 3.2.2. የተገልጋዮች የመቆያ ቦታ/waiting room/ እና መስተንግዶ ስታንዳርድ

የተገልጋዮች የመቆያ ቦታና መስተንግዶ በሚከተለው ስታንዳርድ መሠረት መፈፀም አለበት፡-

ሀ) የተገልጋዮች መቆያ ቦታ ፅዱና ምቹ መሆን አለበት፤

ለ) የተገልጋዮች መቆያ ቦታ ተገልጋዮችን መሰረት በማድረግ የሚዘጋጅ ሆኖ የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁሉም ተገልጋዮች ተደራሽ መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) በተገልጋዮች መቆያ ቦታ ላይ እና በመገልገያ ክፍሎች ውስጥ ስለአገልግሎት አሰጣጡ እና ስለተገልጋዮች ግዴታ የሚያስረዱ ብሮሸሮች እና ሌሎች ጠቃሚና ወቅታዊ መረጃዎች በሚታይና ተደራሽ በሆነ ቦታ መቀመጥ/መለጠፍ አለባቸው፤

መ) የወረፋ ማስያዣ ካርዶች ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች እንደ የአመጣጣቸው ቅደም ተከተል መሰረት አገልግሎት መሰጠት አለበት፤

ሠ) የተገልጋዮች መቆያ ቦታ ተገልጋዮች አገልግሎት ለማግኘት ሲጠባበቁ የሚቀመጡበት በአንድ ጊዜ ቢያንስ 5 ተገልጋይ ሊያስቀምጡ የሚችሉ ወንበሮች ሊኖራቸው ይገባል፤

ረ) በተገልጋዮች መቆያ ቦታ ላይ ተገልጋዮች ስለ አገልግሎት አሰጣጡ አስተያየት የሚሰጡበት መዝገብ፣ የአስተያየት መስጫ ሳጥንና እስክሪብቶ ሊቀመጥ ይገባል፤

ሰ) በህዝብ መጸዳጃና በገላ መታጠቢያ ቤቶች መግቢያ አካባቢ ለልዩ ልዩ መረጃዎች መለጠፊያ የሚያገለግል የማስታወቂያ ሰሌዳ መኖር አለበት፤

ሸ) ተገልጋዮች በህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ውስጥ ጫት መቃም፣ ሲጃራ ማጨስ እና ሌሎች ለህዝብ ጤና ጠንቅ የሆኑ ተግባራትን መፈፀም እንደሌለባቸው መልዕክት አስተላላፊ በራሪ ጽሑፎች /fliers/ ተዘጋጅተው ተገልጋዮች ሊያነቡት በሚችሉበት ቦታ መቀመጥ አለባቸው፤

ቀ) ተገልጋዮች ደረቅ ቆሻሻን በህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ውሃ ማፋሰሻዎች ውስጥ መጣል እንደሌለባቸው፣ ማንኛውንም ዓይነት ጽሑፍ በግድግዳ ላይ መጻፍና ቆሻሻ መቀባት እንደሌለባቸው፣ በመገልገያ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶችን ለተገቢው አገልግሎት ብቻ መጠቀም እንዳለባቸው፣ የመገልገያ ቁሳቁሶችን ሆን ብሎ ማበላሸትና ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሌለባቸው መልዕክት ማስተላለፊያ ብሮሸሮች ተዘጋጅተው በተገልጋዮች መቆያ ቦታ/waiting room/ እና በመገልገያ ክፍሎች ውስጥ መቀመጥ/በሚታይ ቦታ መለጠፍ አለባቸው፤

## 3.3. በህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት መስጫ ቤቶች ውስጥ መሟላት ያለባቸው ቁሳቁሶች

በህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት መስጫ ቤቶች ውስጥ ቢያንስ የሚከተሉት ቁሳቁሶች ማሟላት አለባቸው

ሀ) የመጸዳጃ ወረቀት/soft paper/፣

ለ) በሁሉም የመጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ውስጥ እንዲሁም በእጅ መታጠቢያ አቅራቢያ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት/waste bins/፣

ሐ) የገላና የእጅ መታጠቢያ ሳሙና፣

መ) የእጅ ማድረቂያ ፎጣ እንደአስፈላጊነቱ የወረቀት ፎጣ/paper towel/፣

ሠ) ለገላ መታጠቢያ ክፍል ነጠላ ጫማ እና አንድ ፕላስቲክ ወንበር፣

ረ) ለፅዳትና ውበት ስራዎች የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች የቁም መጥረጊያ፣ መወልወያ፣ የመጸዳጃ ቤት ብሩሽ፣ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት/waste bin/ እና ገንዳ፣ የእጅ ጋሪ፣ መቧጠጫ/ሬክ/፣ ማጭድ፣ ዶማ፣ የውሀ ማጠጫ የላስቲክ ቱቦ፣ ሳሙና፣ አሞ፣ መጥፎ ሽታንና ተህዋስያንን የሚያስወግዱ እንዲሁም መልካም መዓዛ የሚፈጥሩ የጽዳት ኬሚካሎች/detergents & disinfectants/፣ ሊሟሉ ይገባል፡፡

## 3.4. የጽዳትና ውበት እና የጤና አጠባበቅ ስታንዳርድ

ሀ) በማናቸውም ጊዜ የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች፣ የወንዶች የሽንት መጠቀሚያ አካፋዮች፣ የእጅ መታጠቢያዎችና የተገልጋይ መቆያ ቦታዎች ንፁህ ሆነው ለተገልጋይ መቅረብ አለባቸው፤

ለ) በማናቸውም ሁኔታ የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች ያለውሃ አገልግሎት መስጠት የለባቸውም፤

ሐ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች አንድ ተገልጋይ ከተጠቀመ በኋላ ለሚቀጥለው ተገልጋይ ንጹህ ሆነው መጠበቅ አለባቸው፤

## 3.5. የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

ሀ) በተቀመጠው የአገልግሎት መስጫ ሰዓት ውስጥ ተገኝቶ መጠቀም፤

ለ) የአገልግሎት ክፍያ መክፈል፣

ሐ) ወረፋ በስርዓት መጠበቅና ማክበር፤

መ) ከ6 ኪሎ ግራም በላይ ክብደት ያለው እቃ ይዞ ወደ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ክፍሎች አለመግባት፤

# 4. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ አስተዳደር /Management/ ስታንዳርድ

## 4.1. ጠቅላላ መሥፈርት

ሀ) የከተማ አስተዳደሩ ለህዝብ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ ቤቶች ግንባታ የሚውል የለማና ከይገባኛል ነጻ የሆነ ቦታ ማቅረብ አለበት፤

ለ) የከተማ አስተዳደሩ ለህዝብ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ ህንፃዎች አስፈላጊውን ጥበቃ፣ ጥገናና እድሳት ማድረግ አለበት፤

ሐ) የከተማ አስተዳደሩ ከህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚከፈሉ ክፍያዎችን (ለኤሌክትሪክና ለውሃ ፍጆታ፣ ለፍሳሽ ማስነሻ እንዲሁም ለጥገና፣ ለእድሳት፣ ለጽዳት፣ ጥበቃና ለመሳሰሉት የሚያስፈልገውን ወጪ) መሸፈን አለበት፤

መ) አገልግሎት ሰጪው ተቋም በሥራው ያሰማራቸውን ሰራተኞች ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ ለሰራተኞቹም በስታንዳርዱ መሰረት የደህንነትና የንፅህና መጠበቂያ አልባሳትና መሳሪያዎች በወቅቱ ማቅረብ፣ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች በስራ ወቅት የግል ደህንነት መከላከያ አልባሳትንና ቁሳቁሶችን በተገቢው ሁኔታ ስለመጠቀማቸው መከታተል እና ለመጸዳጃ እና ለገላ መታጠቢያ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ አላቂና ቋሚ ዕቃዎችን ማቅረብ አለበት፤

ሠ) አገልግሎት ሰጪው ተቋም የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶችን በወቅቱ መጠገንና ደህንነታቸውን መጠበቅ፣ የፍሳሽ ቆሻሻን ከማጠራቀሚያው /septic tank/ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በወቅቱ ማስነሳት አለበት፣

ረ) አገልግሎት ሰጪው ተቋም ከከተማ አስተዳድሩና ከሌሎች የሚመለከተቸው ተቋማት ተቆጣጣሪዎች በሚመጡበት በማናቸውም ጊዜ መረጃ መስጠትና ማሳየት አለበት፣

ሰ) አገልግሎት ሰጪው ተቋም የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት የተደራጁና አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን በየወቅቱ መከታተል፣ መቆጣጠርና ወቅታዊ ግብረ-መልስ መስጠት አለበት፤

ሸ) አገልግሎት ሰጪው ተቋም ለህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች አስፈላጊ የመሰረተ ልማት/መብራት፣ ውሃ፣ መንገድና የመሳሰሉትን/መዘርጋት አለበት፤

ቀ) ተቋሙ ለአገልግሎት ሰጪዎች የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና እርዳታ አሰጣጥን ጨምሮ አግባብነት ያለው ስልጠና እና ግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት አለበት፤

በ) ተቋሙ በአገልግሎት አሰጣጡ ዙሪያ በተጠቃሚዎች እና በአካባቢው ነዋሪዎች ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ መስጠት ይኖርበታል፤

ተ) ተቋሙ የፍሳሽ ቆሻሻ ማንሻ ተሽከርካሪ በሚፈለገው ሰዓት እንዲቀርብ ማመቻቸት አለበት፤

## 4.2. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ባለቤትነት

ሀ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች በአገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚተዳደሩ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ተቋሙ በውል ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን በማስተላለፍ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ይችላል፤

ለ) በውል የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶችን እንዲያስተዳድሩ የተላለፈላቸው አካላት የማስተዳደሩን ሥራ በሙሉ ሀላፊነት ሊያከናውኑ ይገባል፤

## 4.3. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የቁልፍ አያያዝ

የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የዋናው መግቢያ በር የቁልፍ መክፈቻ በአገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች መያዝ አለበት፤

## 4.4. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የአገልግሎት መጠቀሚያ ታሪፍ

ሀ) የከተማ አስተዳደሩ ለህዝብ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ አገልግሎት ታሪፍ መወሰንና እንዳስፈላጊነቱ መከለስ አለበት፤

ለ) ለህዝብ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ አገልግሎት የክፍያ ታሪፍ ከተማ አስተዳደሮች በሚወስኑት መሰረት ሆኖ የተጠቃሚውን የኢኮኖሚ አቅም ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፤

ሐ) የሚተመነው የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ ቢያንስ ለተገልጋዩ የሚቀርበውን የመጸዳጃ ወረቀት፣ የእጅ ማድረቂያ ፎጣና ወረቀት (paper towel/፣ የገላ መታጠቢያ ሳሙና ወጪን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፤

መ) የሚተመነው የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ ተገልጋይ ሊያየው በሚችል ቦታ በግልጽ መለጠፍ አለበት፤

ሠ) ተገልጋይ ለሚከፍለው ክፍያ ደረሰኝ ሊሰጠው ይገባል፤

## 4.5. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የሰው ኃይል

አገልግሎት ሰጪው አካል ለህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት የሚሰጡ በያንዳንዱ የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች 1 ገንዘብ ተቀባይ፣ ቢያንስ 1

የፅዳት ሰራተኛ እና 1 የጥበቃንና የአትክልተኝነት ሥራ ደርቦ የሚሠራ ሠራተኛ መሟላት አለበት፤

## 4.6. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ዕቅድ

የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የሚያስተዳድሩ አካላት ለሥራ ማስኬጃ፣ ለፅዳትና ውበት፣ ለአልባሳት፣ ለቁሳቁስ ግዢ፣ ለጥገና፣ ለፍሳሽና ለደረቅ ቆሻሻ ማስነሻ፣ ለውሃና ለመብራት ፍጆታ ወዘተ በጀት በዕቅድ መያዝ አለባቸው፤

## 4.7. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ክትትልና ቁጥጥር

በህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች በተቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎቱ እየቀረበ ስለመሆኑ የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚመለከታቸው አካላት በየዕለቱ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለባቸው፤

## 4.8. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የመረጃ አያያዝ

ሀ) ተጠቃሚዎችን በማያስቸግር ሁኔታ ስለተጠቃሚዎች መረጃ በየዕለቱ በጾታና በተጠቃሚው ዓይነት ተመዝግቦ መያዝ አለበት፤

ለ) ከህዝብ መጸዳጃና ከገላ መታጠቢያ አገልግሎቶች የሚነሳው ፍሳሽ ቆሻሻ መጠን በየጊዜው መረጃ መያዝ አለበት፤

## 4.9. የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት

የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት አሰጣጥን የሚከታተልና የሚመራ አደረጃጀት በአገልግሎት ሰጪው ጽ/ቤቱ ደረጃ ሊኖር ይገባል፡፡

## 4.10. የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በሚከተለው ስታንዳርድ መሠረት መፈፀም አለበት፡፡

ሀ) ከመጸዳጃና ከገላ መታጠቢያ ቤቶች የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ በየዕለቱ መነሳትና ወደ ጊዜያዊ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ መወሰድ ወይም መወገድ አለበት፤

ለ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ /septic tank/ ለመሙላት 0.50 ሜትር ሲቀረው በፍሳሽ ማንሻ ተሽከርካሪ /vacuum truck/ መነሳት አለበት፤

ሐ) በማናቸውም ሁኔታ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያው ሞልቶ አገልግሎት ማስተጓጎልም ሆነ ወደ ውጪ መፍሰስ የለበትም፤

### 4.11. የአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች የግል ደህንነትና ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች /personal protective equipment/

የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ቢያንስ የሚከተሉት የግል ደህንነት መከላከያ አልባሳትና ቁሳቁሶች ሊሟላላቸው ይገባል፡፡

ሀ) የደህንነት ጫማ ወይም ቦት፣ ባለማንገቻ ቱታ /ካፖርት/ ሸርጥ/፣ የደንብ ልብስ፣ ጠንካራ ጓንቶች፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ /ማስክ/ እና የእጅ ባትሪ፤

ለ) የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጫ ሳጥን/first aid kit/ ፤

ሐ) ለአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች የንፅህና መጠበቂያ ቢያንስ ሳሙና፣ ኦሞ፣ ሶፍት የመሳሰሉት ቁሳቁሶች መሟላት አለባቸው፤

### 4.12. የአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ጤና አጠባባቅ

ሀ. ለአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ (በየስድስት ወሩ) የጤና ምርመራ ሊደረግላቸው ይገባል፤

ለ. የአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች የጤና ኢንሹራንስ ሊኖራቸው ይገባል፤

## 5. የህዝብ መፀዳጃ እና የገላ መታጠቢያ የህንፃው የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርድ

### 5.1. ጠቅላላ መሥፈርት

የህዝብ መፀዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ህንፃ ግንባታ ሲከናወን ከሚከተሉት ስታንዳርዶች አንፃር መፈፀም አለበት፡፡

ሀ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ሲገነባ አቀማመጡና አቅጣጫው በቀላሉ ተደራሽ፣ ለእይታ ግልጽ የሆነ፣ ለተጠቃሚዎች ደህንነት አመቺነት ያለው እንዲሁም የተፈጥሮ ብርሃንና የአየር ዝውውር ያለው እንዲሆን መደረግ አለበት፤

ለ) ማንኛውም የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የውሃ መስመር ሊዘረጋለት የሚገባ ሲሆን የውሃ አቅርቦቱ እንዳይቋረጥ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ሊገጠምለት ይገባል፤

ሐ) የሚገጠመው ታንከር ውኃ የመያዝ አቅሙ የቀጥታ መስመር ውኃ በሚቋረጥበት ጊዜ ቢያንስ ለ24 ሰዓት አገልግሎት መስጠት የሚችል መሆን ይኖርበታል፤

መ) የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ከዋናው ህንጻ ጣሪያ ቢያንስ 1 ሜትር ከፍ ብሎና ከወሰን ቢያንስ 1 ሜትር ርቆ ከብረት ወይም ከአርማታ በተሰራ ማማ ላይ መቀመጥ ይገባዋል፤

ሠ) ከማንኛውም የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ/liquid waste/ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር/sewer system/ ባለበት አካባቢ በቀጥታ ከመስመሩ ጋር መያያዝ አለበት፤ መስመሩ በሌለበት አካባቢ ሴፕቲክ ታንክ ተዘጋጅቶ ወደ ሴፕቲክ ታንኩ እንዲፈስ መደረግ ይኖርበታል፤

ረ) ማንኛውም ሴፕቲክ ታንክ ሲዘጋጅ የመያዝ አቅሙ ከ27 ሜትር ኪዩብ (3ሜ. ጎን፣ 3ሜ. ስፋትና 3ሜ. ጥልቀት) በታችና ከ64 ሜትር ኪዩብ (4ሜ. ጎን፣ 4ሜ. ስፋትና 4ሜ. ጥልቀት) በላይ መሆን የለበትም፤

ሰ) ማንኛውም ሴፕቲክ ታንክ ሲዘጋጅ ፍሳሽ ወደ ውስጥም ሆነ ወደ ውጭ በማያሰርግ ሁኔታ መሰራት አለበት፤

ሸ) ማንኛውም ሴፕቲክ ታንክ ሲዘጋጅ አየር ማስተንፈሻ /vent/ ሊኖረው ይገባል፤

ቀ) ማንኛውም ሴፕቲክ ታንክ ሲዘጋጅ ከወሰን ቢያንስ 1.5 ሜትረ ርቆ መገንባት አለበት፤

በ) ከማንኛውም ከህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ሜዳ፣ ወደ ጎርፍ ማስወገጃ መስመር /drainage line/ ወይም ወደ ወንዝ መለቀቅ የለበትም፤

ተ) የሕዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ግንባታ ከወሰን 2.5 ሜትር ርቆ መገንባት አለበት፤

ቸ) ማንኛውም የህዝብ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ቤት ለሴቶች፣ ለወንዶችና ለአካል ጉዳተኞች በግልጽ ተለይተው የተዘጋጁ የመጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፤

ጎ) በአውቶቡስ መናኸሪያዎች አካባቢ የሚገነባው ማንኛውም የህዝብ መጸዳጃ ቤት ለሴቶች ቢያንስ 2 የመጸዳጃ ክፍል፣ አንድ የገላ መታጠቢያ ክፍልና አንድ የህጻናት ንጽህና መጠበቂያ ክፍል፤ ለወንዶች ቢያንስ 2 የመጸዳጃ ክፍል፣ ቢያንስ 2 የውኃ ሽንት አካፋይና 1 የገላ መታጠቢያ ክፍል እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች 1 መጸዳጃ ክፍልና 1 መታጠቢያ ክፍል ሊኖረው ይገባል፤

ነ) ከአውቶቡስ መናኸሪያ አካባቢዎች ውጭ የሚገነባው ማንኛውም የህዝብ መጸዳጃ ቤት ለሴቶች ቢያንስ 1 የመጸዳጃ ክፍል፣ አንድ የገላ መታጠቢያ ክፍልና አንድ የህጻናት ንጽህና መጠበቂያ ክፍል፤ ለወንዶች ቢያንስ 1 የመጸዳጃ ክፍል፣ ቢያንስ 2 የውኃ ሽንት አካፋይና 1 የገላ መታጠቢያ ክፍል እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች 1 መጸዳጃ ክፍልና 1 መታጠቢያ ክፍል ሊኖረው ይገባል፤

ኘ) ማንኛውም የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሰራተኞች ቢሮ እና የተገልጋይ ማረፊያ /waiting room/ ሊኖረው ይገባል፤

አ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ህንፃዎች ከዋና መንገድ ርቀው ከተሰሩ የተስተካከለና አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁሉም ተገልጋዮች ምቹ የሆነ መንገድ ሊኖራቸው ይገባል፤

ከ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ህንፃ አካባቢ ለውበትና ለመናፈሻነት በሚያገለግሉ ሳርና አበባዎች ሊተከሉበት ይገባል፤

ኸ) በህዝብ መጸዳጃ ቤትና በገላ መታጠቢያ ዙሪያ የሚተከሉ እጽዋቶች ቁመታቸው ከ0.70 ሜትር በላይ ማደግ የለበትም፤

## 5.2. የቦታ መረጣ/site selection/ ስታንዳርድ

የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ህንፃ ለመገንባት የቦታ መረጣ በሚከተለው ስታንዳርድ መሠረት መፈፀም አለበት፡፡

ሀ) ማንኛውም ለህዝብ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ ቤት የሚመረጥ ቦታ ከአካባቢው የመሬት አጠቃቀም ፕላን ጋር የተጣጣመና በከተማው ፕላን የተፈቀደ መሆን ይገባዋል፤

ለ) ማንኛውም ለህዝብ መጸዳጃነትና ለገላ መታጠቢያ የሚመረጥ ቦታ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ የተከተለ መሆን ይገባዋል፤

ሐ) ማንኛውም ለህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ግንባታ የሚመረጥ ቦታ መሰረተ ልማት (ማለትም ውሃ፣ መብራት፣ መንገድና ተፋሰስ ወዘተ) የተዘረጋለት መሆን ይገባዋል፤

መ) ለህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች ግንባታ የሚመረጥ ቦታ የህዝብ እንቅስቃሴ የሚበዛባቸው አካባቢዎች (ከፍተኛ የትራፊክ እንቅስቃሴ ያለባቸው አካባቢዎች፣ የአውቶብስ መናኸሪያዎች፣ የህዝብ መሰብሰቢያ፣ መናፈሻዎች፣ የህዝብ በዓላት የሚከበሩባቸው ቦታዎች፣ የገበያ ስፍራዎች፣ ህዝብ አዘውትሮ የሚጎበኛቸው ቦታዎች እና የመሳሰሉት) ላይ በቅድሚያ ማተኮር ይኖርበታል፤

ሠ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሚገነባበት ቦታ ከዋናው መንገድ፣ ከገበያ ስፍራ፣ ከአውቶቢስ መናኸሪያ፣ ከታክሲና አውቶቡስ ማቆሚያ/ፌርማታ፣ ከመዝናኛ እና ከመሳሰሉት ቦታዎች ከ500 ሜትር በላይ ወይም ከ5 ደቂቃ የእግር ጉዞ በላይ መራቅ የለበትም፤

ረ) ማንኛውም ለህዝብ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ ቤት ግንባታ የተመረጠ ቦታ ሳይት ፕላንና የይዞታ ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል፤

ሰ) ማንኛውም የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ለጎርፍ እና ውሃ ለማቆር ተጋላጭ በሆነ ቦታ መገንባት የለበትም፤

ሸ) አንድ የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ህንፃ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት እንደሚገነባው ህንጻ መጠን የሚወሰን ቢሆንም አነስተኛው የቦታ ስፋት ከ 46.82 ካ.ሜ በታች መሆን የለበትም፤

ቀ) አንድ የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ህንፃ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት እንደሚገነባው ህንጻ መጠን የሚወሰን ቢሆንም የሴፕቲክ ታንክ /Septictank/ መገንቢያ ቦታን ጨምሮ ከ62.82 ካሬ ሜትር በታች መሆን የለበትም፤

## 5.3. የህዝብ መፀዳጀ እና ገላ መታጠቢያ የህንጻው ዋና መግቢያ በር ስታንዳርድ

ሀ) የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ህንጻ ዋና በር ከእንጨት ወይም ከብረት ሊሰራ ይችላል፤

ለ) የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ህንጻ ዋና በር ቀለሙ ብሩህና ከግድግዳው ቀለም የተለየ መሆን አለበት፤

ሐ) የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ህንጻ ዋና በር የተጣራ መግቢያ ስፋት ከ0.90 ሜትር ማነስ የለበትም፤

መ) የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ህንጻ ዋና በር ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽና ምንም ዓይነት መሰናክል የማይፈጥር ሆኖ መዘጋጀት አለበት፤

ሠ) የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ህንጻ ዋና በር ከውጭ መቆለፊያ ሊዘጋጅለት ይገባል፤

ረ) የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ህንጻ ዋና በር በምሽት በግልጽ እንዲታይ መብራት ሊገጠምለት ይገባል፤

## 5.4. የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሰራተኞች ቢሮ/የእንግዳ መቀበያ/reception/፣ የተገልጋይ ማረፊያ፣ የክፍሎች/cubicles/፣ የወንዶች የውኃ ሽንት መጠቀሚያ ቦታ አካፋይ እና የእጅ መታጠቢያ ስታንዳርድ

### 5.4.1. የሰራተኞች ቢሮ፣ የእንግዳ መቀበያ/reception/ እና የተገልጋይ ማረፊያ ቦታ

ሀ) የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሰራተኞች ቢሮ እና የእንግዳ መቀበያ/reception/ ስፋቱ ቢያንስ 1.50 ሜትር በ 1.50 ሜትር መሆን ይገባዋል፤

ለ) የእንግዳ ማረፊያ ክፍል/ቦታ /waiting room/ ስፋቱ ቢያንስ 2 ሜትር በ 2 ሜትር መሆን አለበት፤

### 5.4.2. የህዝብ መጸዳጃ ክፍሎች/cubicles/ ስታንዳርድ

የህዝብ መፀዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ሲገነቡ በሚከተሉት ስታንዳርዶች መሠረት መሆን አለባቸው፡፡

ሀ) አንድ መጸዳጃ ክፍል በቀን ቢያንስ ለ100 ሰዎች አገልግሎት መስጠት እንዳለበት ታሳቢ መደረግ አለበት፤

ለ) አንድ የመጸዳጃ ክፍል ስፋት 0.90 ሜትር በ 1.20 ሜትር መሆን አለበት፤

ሐ) አንድ መጸዳጃ ክፍል የተጣራ የበር ስፋት ከ0.60 ሜትር ያነሰ መሆን የለበትም፤

መ) አንድ የመጸዳጃ ክፍል በር ከወለል 0.15 ሜትር ከፍ ብሎ መገጠም ያለበት ሲሆን ከአናቱ በኩልም በተመሳሳይ ከ0.15 ሜትር ያላነሰ ክፍተት ሊኖረው ይገባል፤

ሠ) አንድ የመጸዳጃ ክፍል በር ከውስጥ ተወርዋሪ መቀርቀሪያ ሊኖረው ይገባል፤ መቀርቀሪያውም በአደጋ ጊዜ በሩን ለመንቀል በሚያስችል ሁኔታ የተዘጋጀ መሆን አለበት፤

ረ) አንድ የመጸዳጃ ክፍል በር ከውስጥ ለልብስ ወይም ቦርሳ መስቀያ ሊገጠምበት ይገባል፤

ሰ) የሚገጠመው መስቀያ ጥንካሬ ያለው ሆኖ እስከ 2 ኪሎ ግራም ድረስ መሸከም የሚችል መሆን አለበት፤

ሸ) የመጸዳጃ ክፍሉ አንዱ ማዕዘን ላይ ለዕቃ ማስቀመጫ የሚሆኑ ቅስቶች/መደርደሪያዎች ሊገጠሙለት ይገባል፤

ቀ) አንድ የህዝብ መፀዳጃ ቤት ካሉት መጸዳጃ ክፍሎች ውስጥ 80 በመቶው ባለ ሳህን/ተርኪሽ እና ቀሪው 20 በመቶ ባለ መቀመጫ መጸዳጃ ሆነው ለወንድም ለሴትም መዘጋጀት አለባቸው፤

በ) የመጸዳጃ ክፍሉ ባለ መቀመጫ ከሆነ መቀመጫው ከ0.57 ሜትር እስከ 0.60 ሜትር ከወለል በላይ ከፍታ ሊኖረው ይገባል፤

ተ) የመጸዳጃ ክፍሉ የመጸዳጃ ቤት ወረቀት ማስቀመጫ ሊገጠምለት ይገባል፤

ቸ) የመጸዳጃ ቤት ወረቀት ማስቀመጫ ሲገጠም በስተግራ ወይም በስተቀኝ ከመሬት 0.70 ሜትር ከፍ ማለት አለበት፤

ኀ) የህዝብ መጸዳጃ ቤት ክፍሎች ግድግዳቸው ውሃ የማያቀርና የማያሰርግ ሆኖ በቀላሉ ሊታጠብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

### 5.4.3. በህዝብ መፀዳጃ ቤቶች የአካል ጉዳተኞች መጸዳጃ ክፍሎች/cubicles/ ስታንዳርድ

በህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች የመጸዳጃ ክፍል ሲገነባ ከላይ በአንቀጽ 5.3.2 በፊደል መ፣ ሠ እና ሸ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የሚከተሉትን ማሟላት ይገባዋል፡-

ሀ) የመጸዳጃ ክፍሉ 1.50 ሜትር በ 1.50 ሜትር ስፋት ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፤

ለ) የመጸዳጃ ክፍሉ የተጣራ የበር ስፋት ከ0.90 ሜትር ማነስ የሌለበት ሆኖ ወደ ውጭ ተካፋች መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) በመጸዳጃ ክፍል ውስጥ በሦስቱም ጎኖች የእጅ መደገፊያ ያለው ሆኖ መደገፊያው ከግድግዳው ከ0.08 ሜትር እስከ 0.10 ሜትር ርቆ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

መ) የመጸዳጃ ክፍሉ መቀመጫ ከ0.57 ሜትር እስከ 0.60 ሜትር ከወለል በላይ ከፍታ ሊኖረው ይገባል፤

ሠ) የእጅ መታጠቢያ፣ ማድረቂያ፣ እና የሳሙና ማስቀመጫ የመጸዳጃ ክፍሉ ውስጥ የሚገጠም ሆኖ ከወለል በላይ ከ0.50 ሜትር እስከ 0.70 ሜትር ከፍታ ላይ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

### 5.4.4. የወንዶች የውሃ ሽንት መጠቀሚያ ቦታ አካፋይ/urinal/ ስታንዳርድ

ሀ) አንድ ለወንዶች የሚዘጋጅ የሽንት መክፊያ በአንድ ጊዜ ለአንድ ሰው ብቻ የሚያገለግል መሆን አለበት፤

ለ) አንድ ነጠላ የሽንት መክፈያ ክፍል 0.70 ሜትር ስፋት ያለውና በግራና በቀኝ እያንዳንዳቸው የ0.75 ሜትር ቁመትና 0.50 ሜትር ወርድ ያላቸው መከለያዎች የተዘጋጀለት መሆን ይገባዋል፤

ሐ) የሽንት መቀበያ ሳህን ከንፈር ከግድግዳው 0.25 ሜትር ወጣ ያለ መሆን አለበት፤

መ) የሽንት መቀበያ ሳህን ከንፈር ከመጸዳጃ ቤቱ ወለል የሚኖረው ከፍታ ከ0.50 ሜትር መብለጥ የለበትም፤

### 5.4.5. የእጅ መታጠቢያ ስታንዳርድ

ሀ) ማንኛውም የህዝብ መጸዳጃ ቤት ለሴቶችና ለወንዶች ተለይቶ የተዘጋጀ የእጅ መታጠቢያ ሊኖረው ይገባል፤

ለ) የእጅ መታጠቢያዎች ባለ ነጠላ ሳህኖች ወይም ባለአግዳሚ ገንዳ ሊሆኑ ይችላሉ፤

ሐ) የነጠላ ሳህኖች መጠን ቢያንስ ርዝመቱ 0.50 ሜትር ወርዱ 0.40 ሜትር መሆን ይገባዋል፤

መ) የእጅ መታጠቢያው ገንዳ ወርዱ 0.40 ሜትር፣ ጥልቀቱ 0.20 ሜትር መሆን ያለበት ሲሆን ርዝመቱ ግን እንደ መጸዳጃ ክፍሎቹ ብዛት ሊወሰን ይችላል፤

ሠ) የውሃ ማፍሰሻው ጫፍ ከግድግዳው 0.20 ሜትር ወጣ ብሎ ውሃ በገንዳው መሃል ላይ እንደሚያፈስ ተደርጎ መሰራት አለበት፤

ረ) የእጅ መታጠቢያ ነጠላ ሳህኑም ሆነ የገንዳው ከንፈር ከመጸዳጃ ቤቱ ወለል የሚኖረው ከፍታ 0.75 ሜትር መሆን ይገባዋል፤

ሰ) አንድ የእጅ መታጠቢያ ነጠላ ሳህን አንድ የፈሳሽ/የደረቅ ሳሙና ማስቀመጫ ሊኖረው ይገባል፤

ሸ) የእጅ መታጠቢያው ገንዳ ከሆነ ቢያንስ በሁለት ማፍሰሻ ቧንቧዎች መሃል አንድ የፈሳሽ/የደረቅ ሳሙና ማስቀመጫ ሊኖረው ይገባል፤

ቀ) ከእጅ መታጠቢያ ሳህን ወይም ገንዳው አጠገብ የእጅ ማድረቂያ ፎጣ ወይም የወረቀት ፎጣ /paper towel dispenser/ ሊኖረው ይገባል፤

### 5.4.6. የህዝብ የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ስታንዳርድ

የህዝብ የገላ መታጠቢያ ክፍሎች የሚከተሉት ስታንዳርዶች ይኖሯቸዋል፡-

ሀ) አንድ የህዝብ መጸዳጃ ገላ መታጠቢያ ቤት ለሴቶች፣ ለወንዶችና ለአካል ጉዳተኞች በግልጽ ተለይተው የተዘጋጁ የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፤

ለ) አንድ የገላ መታጠቢያ ክፍል ስፋት 1.00 ሜትር በ 1.50 ሜትር መሆን ይገባዋል፤

ሐ) የገላ መታጠቢያ ክፍል በር የተጣራ ስፋት ከ0.60 ሜትር ማነስ የለበትም፤

መ) የገላ መታጠቢያ ክፍል በር ከውስጥ ተወርዋሪ መሽንጎሪያ ሊኖረው ይገባል፤ መሽንጎሪያውም በአደጋ ጊዜ በሩን ለመንቀል በሚያስችል ሁኔታ የተዘጋጀ መሆን አለበት፤

ሠ) የገላ መታጠቢያ ክፍል በር ከውስጥ ለልብስ መስቀያ ሊገጠምለት ይገባል፤

ረ) የሚገጠመው የልብስ መስቀያ ጥንካሬ ያለው ሆኖ እስከ 2 ኪሎ ግራም ድረስ መሸከም የሚችል መሆን አለበት፤

ሰ) የገላ መታጠቢያ ክፍሉ ውሃ በማይደርስበት አንዱ ማዕዘን ላይ ለልብስ፣ ለጫማና ለሌሎች ዕቃዎች ማስቀመጫ የሚሆኑ ቅስቶች/መደርደሪያዎች ሊገጠሙለት ይገባል፤

ሸ) የገላ መታጠቢያ ክፍል መስኮት የሚያስፈልገው ሲሆን መስኮቱም የሚገጠመው ከሰው ቁመት ከፍ ብሎ ከወለሉ 2 ሜትር ከፍታ ላይ መሆን ይገባዋል፤

ቀ) የገላ መታጠቢያ ቤቱ መስኮት ከመስታወት መሰራት ያለበት ሲሆን ለአየር ማስገቢያና ማስወጫ ያህል ከአናቱ ላይ ብቻ ዘንበል የሚደረግ መሆን ይገባዋል፤

በ) የገላ መታጠቢያው ውሃ መርጫ /shower head/ ከመታጠቢያው ወለል 2 ሜትር ከፍ ብሎ ግድግዳው ላይ መገጠም አለበት፤

ተ) የውሃ መርጫው /shower head/ ከግድግዳው ከ0.35 ሜትር እስከ 0.40 ሜትር ያላነሰ ወጣ ብሎ በመዘርጋት የመታጠቢው ሳህን መሃል ላይ እንደሚያፈስ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፤

ቸ) የገላ መታጠቢያው ውሃ መርጫ መክፈቻና መዝጊያ ከወለሉ 0.80 ሜትር ከፍ ብሎ መገጠም አለበት፤

ኀ) የገላ መታጠቢያው ክፍል በቀንም ሆነ በማታ በቂ ብርሃን ሊኖረው ይገባል፤

ነ) የገላ መታጠቢያው ክፍል ግድግዳው ላይ ከወለሉ 1 ሜትር ከፍ ብሎ የሳሙናና የቅባት ማስቀመጫ ሊገጠምለት ይገባል፤

ኘ) የገላ መታጠቢያው ክፍል የውስጥ ግድግዳ ውሃ በማያቆርና በማያሰርግ ሁኔታ በሲሚንቶ ወይም በሴራሚክ ሊሰራ ይገባል፤

አ) የገላ መታጠቢያው ክፍል ወለል ለሁለት የሚከፈል ሲሆን ውሃ የሚፈስበት መቆሚያ ከሌላው የወለል ክፍል ከ0.05 ሜትር እስከ 0.10 ሜትር ጎድጎድ ብሎ ውሃ በማያቆርና በማያሰርግ ሁኔታ ሳህን ይገጠምበታል፤ ይህ በማይቻልበት ጊዜ በሴራሚክ ወይም በሲሚንቶ ሊሰራ ይገባዋል፤ ለውሃ መውረጃ በአንዱ ጥግ ራሱን የቻለ ባለ ወንፊት ማስረጊያ ሊኖረው ይገባል፤

ከ) ውሃ በቀጥታ የማያርፍበት ግማሹ ክፍል ውሃ በማያቆር፣ በማያሰርግ ሁኔታና በማያንሸራትት ሴራሚክ ወይም ሲሚንቶ ሊሰራ የሚገባው ሲሆን ውሃ ልኩም ወደ ውሃ ማፋሰሻው በመጠኑ ያጋደለ መሆን አለበት፤

ኸ) በህዝብ የገላ መታጠቢያ ቤቶች ለገላ መታጠቢያ አገልግሎት የሚቀርበው ውሃ ቀዝቃዛ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ሙቅ ሊሆን ይችላል፤

### 5.4.7. በህዝብ መፀዳጃ ቤት የአካል ጉዳተኞች የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ስታንዳርድ

በህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች የገላ መታጠቢያ ክፍል ሲገነባ ከላይ በአንቀጽ 5.3.6 ከፊደል ሀ—ኸ ከተቀመጠው በተጨማሪ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የገላ መታጠቢያ ክፍሉ 1.50 ሜትር በ1.50 ሜትር ስፋት ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፤

ለ) የገላ መታጠቢያ ክፍሉ የተጣራ የበር ስፋት ከ0.90 ሜትር ማነስ የሌለበት ሆኖ ወደ ውጭ ተከፋች መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) የገላ መታጠቢያ ክፍሉ ውስጥ በሦስቱም ጎኖች የእጅ መደገፊያ ያለው ሆኖ መደገፊያው ከግድግዳው ከ0.08 ሜትር እስከ 0.10 ሜትር ርቆ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

#### 5.4.8. የህጻናት ንጽህና መጠበቂያ ክፍል

የህጻናት ንጽህና መጠበቂያ ክፍል ስፋቱ ከ1 ሜትር በ1.20 ሜትር ያለነሰ ሆኖ በውስጡም ለህጻናት ማጸዳጃና ልብስ መቀየሪያ ጠረጴዛና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ሊኖረው ይገባል፤

# ክፍል ሁለት፡-የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የአገልግሎት፣ የአስተዳደር እና የህንፃው የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርድ

## 6. የአገልግሎት ስታንዳርድ

ለጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የሚከተሉት የአገልግሎት ስታንዳርዶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

ሀ) ማንኛውም የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ተጠቃሚ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቱን ጽዳት በሚያጸዳበት ወቅት በስታንዳርዱ አንቀጽ 7.3.2 በተገለፀው መሰረት የደህንነትና የንጽህና መጠበቂያ አልባሳትና መሳሪያዎችን መጠቀም አለበት፤

ለ) ማንኛውም የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች አንድ ተጠቃሚ ከተጠቀመ በኋላ ለሚቀጥለው ተጠቃሚ ክፍሎቹን ንጹህ በማድረግ ማስተላለፍ አለበት፤

## 7. የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት የአስተዳደር ስታንዳርድ

### 7.1. ጠቅላላ መሥፈርት

ለጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት የሚከተሉት የአስተዳደር ስታንዳርዶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

ሀ) የከተማ አስተዳደሩ ለጋራ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ ቤቶች ግንባታ የሚውል የለማና ከይገባኛል ነጻ የሆነ ቦታ ማቅረብ አለበት፤

ለ) የከተማ አስተዳደሩ የግል መፃዳጃ ቤቶች  በሌሉባቸው በተፋፈጉ የመኖሪያ አካባቢዎች የጋራ መፀዳጃ እና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ አለበት፤

ሐ) የከተማ አስተዳደሩ አገልግሎቱ ለተዘጋጀላቸው ለሁሉም ተጠቃሚዎች በፍትሃዊነት ተደራሽ እና እንዲሁም የአካባቢው ንጽህና ሁልጊዜ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

መ) ተጠቃሚው ህብረተሰብ ከጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚከፈሉ ክፍያዎችን (የኤሌክትሪክና ውሃ ፍጆታ እንዲሁም የፍሳሽ ማስነሻ ክፍያዎችን) መሸፈን አለበት፤

ሠ) ለጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የ24 ሰዓት ሽፋን ያለው የመብራት አቅርቦት መኖር አለበት፤

ረ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ተጠቃሚዎች በሚያወጡት የጽዳትና ውበት መርሀግብር መሰረት አጠቃላይ የጽዳትና ውበት ስራ ማከናወን አለባቸው፤

ሰ) ተጠቃሚው ህብረተሰብ ለጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ህንጻዎች ወቅቱን ጠብቆ አስፈላጊውን ጥገናና እድሳት ማድረግ አለበት፤

ሸ) ማንኛውም የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ተጠቃሚ ለተፈላጊ የመሰረተ ልማት (ውሃ፣ መብራት) አገልግሎት ክፍያዎች እና ሌሎች ወጪዎች በጋራ ለሚወሰኑ መዋጮዎች በጋራ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ በወቅቱ ማዋጣት አለበት፤

ቀ) የመዋጮው መጠን በጋራ የሚወሰን ሆኖ የተጠቃሚውን ብዛትና እያንዳንዱን ተጠቀሚ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፤

በ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ተጠቃሚዎች የፍሳሽ ቆሻሻን ከማጠራቀሚያው /septic tank/ በአንቀጽ 4.10 በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በወቅቱ ማስነሳት አለባቸው፤

ተ) የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት እንዳይቋ ረጥ  ተጠቃሚዎቹ የመጠባበቂያ ውኃ ማከማቻ ታንከር ማዘጋጀት አለባቸው፤

ቸ) ተጠቃሚዎች የከተማ አስተዳደሩ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ተቋም ተቆጣጣሪዎች በሚመጡበት በማናቸውም ጊዜ መረጃ የመስጠትና የማሳየት ግዴታ አለባቸው፤

ነ) ማንኛውም ተጠቃሚ ዋናውን በር ከውስጥም ሆነ ከውጭ ከቆለፈ በኋላ ቁልፉን ማንሳት አለበት፤

ኘ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ወይም መጠቀሚያ ክፍል ቁልፍ የጣለ/የጠፋበት መተካት አለበት፤

 አ) የሚመለከተው ተቋም ለተጠቃሚዎች የጋራ አጠቃቀምንና ንጽህና አያያዝን በተመለከተ ግንዛቤ ማስጨበጥ አለበት፤

ከ) የሚመለከተው ተቋም በከተማው ስለሚገኙ የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ወቅታዊ መረጃዎች ማሰባሰብ፣ ማደራጀትና መያዝ አለበት፤

## 7.2. የጽዳትና ውበት አጠባበቅ ስታንዳርድ

ለጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት የሚከተሉት የፅዳትና ውበት አጠባበቅ ስታንዳርዶች ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

ሀ) በማንኛውም ሁኔታ የጋራ መጸዳጃ ቤቶች ያለውሃ አገልግሎት መስጠት የለባቸውም፤

ለ) በማናቸውም ጊዜ የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች፣ የእጅ መታጠቢያዎች እና አካባቢው ንጹህ ሆነው መገኘት አለባቸው፤

## 7.3. የጽዳትና ውበት ስራዎችና የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች

ከላይ በንዑስ አንቀፅ 3.3 ለህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ለጽዳትና ውበት ስራዎች እንዲሟሉ የተጠቀሱት የስራ መሳሪያዎች በተመሳሳይ ለጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት መሟላት አለባቸው፡፡

### 7.3.1. የጽዳትና ውበት ስራዎች

ሀ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶችን የማጽዳትና የማስዋብ ስራ በተጠቃሚዎቹ መከናወን አለበት፤

ለ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች አንድ ተጠቃሚ ከተጠቀመ በኋላ ለሚቀጥለው ተጠቃሚ ንጹህ ሆነው መተላለፍ አለባቸው፤

ሐ) ተጠቃሚዎች የድርጊት መርሀ-ግብር አዘጋጅተው የጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤታቸውን ቢያንስ በሳምንት 2 ቀን ማጽዳትና ማስዋብ ይኖርባቸዋል፤

### 7.3.2. የግል ደህንነትና ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች

ለጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች ቢያንስ የሚከተሉት የግል ደህንነት መከላከያ እና የንፅህና መጠበቂያ አልባሳትና ቁሳቁሶች ሊሟላላቸው ይገባል፡፡

ሀ) የደህንነት ጫማ ወይም ቦት፣ ባለማንገቻ ቱታ /ካፖርት/ ሽርጥ/፣ ጠንካራ ጓንቶች፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ /ማስክ/፤

ለ) የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጫ ሳጥን/first aid kit/፤

ሐ) የንፅህና መጠበቂያ ቢያንስ ሳሙና፣ ኦሞ፣ ሶፍት፣ መጥረጊ ሽታንና ተህዋስያንን የሚያስወግዱ እንዲሁም መልካም መዓዛ የሚፈጥሩ የጽዳት ኬሚካሎች /detergents & disinfectants/፤

መ) በእያንዳንዱ የገላ መታጠቢያ ክፍል ውስጥ አንድ የፕላስቲክ ወንበር፤

### 7.3.3. የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ባለቤትነት

ሀ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ተጠቃሚዎቹ በባለቤትነት ይዘው የሚያስተዳድሩት ይሆናል፤

ለ) በውል የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶችን እንዲጠቀሙበት የተላለፈላቸው ነዋሪዎች የማስተዳደሩን ሥራ በሙሉ ኃላፊነት ሊያከናውኑ ይገባል፤

### 7.3.4. የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የቁልፍ አያያዝ

ሀ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የዋናው መግቢያ በር ቁልፍ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የቁልፍ መክፈቻውም በመጸዳጃ ቤቶቹ የሚጠቀሙ ሁሉም አባወራዎች/እማወራዎች ሊኖራቸው ይገባል፤

ለ) የአንድ የጋራ መጸዳጃ ወይም የገላ መታጠቢያ ክፍል ቁልፍ መያዝ ያለበት በክፍሉ እንዲጠቀሙበት በተመደቡ አባወራዎች/እማወራዎች ብቻ ነው፤

ሐ) በማንኛውም ሁኔታ የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የዋናው በር እና የመጠቀሚያ ክፍሎች የመክፈቻ ቁልፎች በር ላይ መተው የለባቸውም፤

መ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ወይም የመጠቀሚያ ክፍሎች ቁልፍ ቢጠፉ በሮችን ወይም ቁልፎችን መገንጠል ክልክል ነው፤

### 7.3.5. የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች የመጠቀሚያ ወጪ

የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤትን ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ወጪ (ለውሃ፣ ለመብራት፣ ለፍሳሽ ማስነሻ፣ ለጥገና፣ ለጽዳትና

ውበት ወዘተ) ሁሉም ተጠቃሚዎች በእኩል መዋጮ በጋራ የሚሸፍኑት ይሆናል፡፡

### 7.3.6. የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ክትትልና ቁጥጥር

የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች በተቀመጠላቸው የአገልግሎት ስታንዳርድ መሰረት ተጠቃሚዎች እየተገለገሉ ስለመሆኑና መጸዳጃ ቤቶቹ በንጽህናና በአግባቡ ስለመያዛቸው የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለባቸው፡፡

### 7.3.7. ተቋማዊ አደረጃጀት

የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት አሰጣጥን የሚከታተልና የሚመራ አደረጃጀት በአገልግሎት ሰጪው ተቋም ደረጃ ሊኖር ይገባል፡፡

## 7.4. የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

ከላይ በንዑስ አንቀፅ 4.10 ከፊደል "ሀ" - "ሐ" ለህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የተቀመጡ ስታንዳርዶች በተመሳሳይ ለጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች መተግበር አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፡-

ከማንኛውም የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ እስከሚወገድ ድረስ ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ /waste bin/ ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል፤

# 8. የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ የህንፃው የውስጥ መገልገያዎች ስታንዳርድ

## 8.1. ጠቅላላ መሥፈርት

ለጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግለት የሚገነባው ህንፃ  የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡፡

ሀ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ሲገነባ አቀማመጡና አቅጣጫው በቀላሉ ተደራሽ፣ ለእይታ ግልጽ የሆነ፣ ለተጠቃሚዎች ደህንነት አመቺነት ያለው እንዲሁም የተፈጥሮ ብርሃንና የአየር ዝውውር ያለው እንዲሆን መደረግ አለበት፤

ለ) ማንኛውም የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የውሃ መስመር ሊዘረጋለት የሚገባ ሲሆን የውሃ አቅርቦቱ እንዳይቋረጥ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ሊገጠምለት ይገባል፤

ሐ) የሚገጠመው የውኃ ታንከር ውኃ የመያዝ አቅሙ የቀጥታ መስመር ውኃ በሚቋረጥበት ጊዜ ቢያንስ ለ24 ሰዓት አገልግሎት መስጠት የሚችል መሆን ይኖርበታል፤

መ) የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ከዋናው ህንጻ ጣሪያ ቢያንስ 1 ሜትር ከፍ ብሎና ከወሰን ቢያንስ 1 ሜትር ርቆ ከብረት ወይም ከአርማታ በተሰራ ማማ ላይ መቀመጥ ይገባዋል፤

ሠ) ከማንኛውም የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ/liquid waste/ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር/sewer system/ ባለበት አካባቢ በቀጥታ ከመስመሩ ጋር መያያዝ አለበት፤ መስመሩ በሌለበት አካባቢ ሴፕቲክ ታንክ ተዘጋጅቶ ወደ ሴፕቲክ ታንኩ እንዲፈስ መደረግ ይኖርበታል፤

ረ) ማንኛውም ሴፕቲክ ታንክ ሲዘጋጅ የመያዝ አአቅሙ ከ27 ሜትር ኪዩብ (3ሜ. ጎን፣ 3ሜ. ስፋትና 3ሜ. ጥልቀት) በታችና ከ64 ሜትር ኪዩብ (4ሜ. ጎን፣ 4ሜ. ስፋትና 4ሜ. ጥልቀት) በላይ መሆን የለበትም፤

ሰ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ግንባታ ከወሰን 2.5 ሜትር ርቆ መገንባት አለበት፤

ሸ) ማንኛውም የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የእጅ መታጠቢያ ሊኖረው ይገባል፡፡

ቀ) ማንኛውም የጋራ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ቤት ለሴቶች፣ ለወንዶችና ለአካል ጉዳተኞች በግልጽ ተለይተው የተዘጋጁ የመጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፤

በ) ከሚሰሩት የጋራ መጸዳጃ እና ገላ መታጠቢያ ክፍሎች/cubicles/ አንዱ ክፍል አካል ጉዳተኞችን ሊያስተናግድ በሚችል መልክ መገንባት አለበት፤

ተ) ማንኛውም የጋራ መጸዳጃ ቤት ቢያንስ 2 የመጸዳጃ ክፍልና አንድ የገላ መታጠቢያ ክፍል ሊኖረው ይገባል፤ የገላ መታጠቢያውና አንዱ የመፀዳጃ ክፍል ለአካል ጉዳተኞችም እንደሚያገለግል ሆኖ መሰራት አለበት፤

## 8.2. የቦታ መረጣ/site selection/ ስታንዳርድ

የጋራ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ህንፃ ለመገንባት የቦታ መረጣ በሚከተለው ስታንዳርድ መሠረት መፈፀም አለበት፡፡

ሀ) ማንኛውም ለጋራ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ አገልግሎት ህንፃ ግንባታ የሚመረጥ ቦታ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ የተከተለ መሆን ይገባዋል፤

ለ) ማንኛውም ለጋራ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ ቤት ግንባታ የሚመረጥ ቦታ መሰረተ ልማት (ውሃ፣ መብራት፣ መንገድና ተፋሰስ ወዘተ) የተዘረጋለት መሆን ይገባዋል፤

ሐ) ማንኛውም ለጋራ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ ቤት ግንባታ የተመረጠ ቦታ ሳይት ፕላንና የይዞታ ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል፤

መ) ማንኛውም የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ለጎርፍ እና ውሃ ለማቆር ተጋላጭ በሆነ ቦታ መገንባት የለበትም፤

ሠ) ማንኛውም ለጋራ መጸዳጃና ለገላ መታጠቢያ ቤት ግንባታ የሚመረጥ ቦታ የተጠቃሚውን አዎንታ ያገኘ፣ ከአካባቢው የመሬት አጠቃቀም ፕላን ጋር የተጣጣመና በከተማው ፕላን የተፈቀደ መሆን ይገባዋል፤

ረ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት በተፋፈጉና የግል መፀዳጃ ለመገንባት የቦታ ጥበት ባለባቸው በመኖሪያ ሰፈሮች/residential area/ ውስጥ ብቻ መገንባት ይኖርበታል፤

ሰ) የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የሚገነባበት ቦታ ከተጠቃሚዎች መኖሪያ ቤት እጅግ ቢበዛ ከ100 ሜትር በላይ መራቅ የለበትም፤

ሸ) ማንኛውም ለጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤት ግንባታ የተመረጠ ቦታ በአገልግሎት ሰጪው ተቋም ስም ሳይት ፕላንና የይዞታ ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል፤

ቀ) ማንኛውም የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ለጤና ደህንነት ሲባል ከመኖሪያ ቤትና ከሌሎች ተቋማት ቢያንስ 2.5 ሜትር መራቅ አለበት፤

በ) አንድ የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ግንባታው የሚያርፍበት ቦታ ስፋት እንደሚገነባው ህንጻ መጠን የሚወሰን ቢሆንም አነስተኛው የቦታ ስፋት ከ11.70 ካ.ሜ. በታች መሆን የለበትም፤

ተ) አንድ የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ግንባታው የሚያርፍበት ቦታ ስፋት እንደሚገነባው ህንጻ መጠን የሚወሰን ቢሆንም አነስተኛው የቦታ ስፋት ሴፕቲክ ታንክ /Septictank/ መገንቢያ ቦታን ጨምሮ ከ20.70 ካ.ሜ. በታች መሆን የለበትም፤

### 8.3. የህንጻው ዋና በር ስታንዳርድ

የጋራ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ህንጻ ዋና በር የሚከተሉት ስታንዳርዶች ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡ የህንጻው ዋና በር፡-

ሀ) ከእንጨት ወይም ከብረት ሊሰራ ይችላል፤

ለ) ቀለሙ ብሩህና ከግድግዳው ቀለም የተለየ መሆን አለበት፤

ሐ) የተጣራ መግቢያ ስፋት ከ0.90 ሜትር ማነስ የለበትም፤

መ) ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽና ምንም ዓይነት መሰናክል የማይፈጥር ሆኖ መዘጋጀት አለበት፤

ሠ) በሰረገላ የሚሰራ ቁልፍ ሊዘጋጅለት ይገባል፤

ረ) በምሽት በግልጽ እንዲታይ መብራት ሊገጠምለት ይገባል፤

## 8.4.የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የክፍሎች /cubicles/ እና የእጅ መታጠቢያ ስታንዳርድ

### 8.4.1. የጋራ መጸዳጃ ክፍሎች /cubicles/ ስታንዳርድ

ለጋራ መጸዳጃ ክፍሎች የሚከተሉት ስታንዳርዶች ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡-

ሀ) አንድ የመጸዳጃ ክፍል በር ከውስጥ ተወርዋሪ መሸንጎሪያ ሊኖረው ይገባል፤መሸንጎሪያውም በአደጋ ጊዜ በሩን ለመንቀል በሚያስችል ሁኔታ የተዘጋጀ መሆን አለበት፤

ለ) የመጸዳጃ ክፍሉ ባለ መቀመጫ ከሆነ መቀመጫው ከ0.57 ሜትር እስከ 0.60 ሜትር ከወለል በላይ ከፍታ ሊኖረው ይገባል፤

ሐ) የመጸዳጃ ክፍሉ የመጸዳጃ ቤት ወረቀት ማስቀመጫ ሊገጠምለት ይገባል፤

መ) የመጸዳጃ ቤት ወረቀት ማስቀመጫ ሲገጠም በስተግራ ወይም በስተቀኝ ከመሬት 0.70 ሜትር ከፍ ማለት አለበት፤

ሠ) የጋራ መጸዳጃ ቤት ክፍሎች ግድግዳቸው ውሃ የማያቀርና የማያሰርግ ሆኖ በቀላሉ ሊታጠብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ረ) እያንዳንዱ የጋራ መጸዳጃ ክፍል /cubicles/ ቢበዛ ለ2 አባወራ/እማወራ ብቻ የሚያገለግል መሆን አለበት፤

ሰ) የጋራ መጸዳጃ ክፍል /cubicle/ ስፋት 0.90 ሜትር በ 1.20 ሜትር ሆኖ የበሩ የተጣራ ስፋት ከ0.60 ሜትር ማነስ የለበትም፤

ሸ) አንድ የጋራ የመጸዳጃ ክፍል በር ከወለል 0.10 ሜትር ከፍ ብሎ መገጠም ያለበት ሲሆን ከአናቱ በኩልም በተመሳሳይ ከ0.10 ሜትር ያላነሰ ክፍተት ሊኖረው ይገባል፤

ቀ) አንድ የጋራ መጸዳጃ ክፍል በር ከውጭ ተንጠልጣይ መቆለፊያ ቁልፍ ሊኖረው ይገባል፤

ሰ) የጋራ መጸዳጃ ክፍል መስኮት የሚያስፈልገው ሲሆን መስኮቱም የሚገጠመው ከሰው ቁመት ከፍ ብሎ ከወለሉ 2 ሜትር ከፍታ ላይ መሆን ይገባዋል፤

ሸ) የጋራ መጸዳጃ ክፍሉ መስኮት ከመስታወት መሰራት ያለበት ሲሆን ለአየር ማስገቢያና ማስወጫ ያህል ከአናቱ ላይ ብቻ ዘንበል የሚደረግ መሆን ይገባዋል፤

### 8.4.2. በጋራ መፀዳጃ ቤቶች የአካል ጉዳተኞች መጸዳጃ ክፍል/cubicles/ ስታንዳርድ

በጋራ መፀዳጃ ቤቶች የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ተደርጎ የሚሰራው መጸዳጃ ክፍል የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የመጸዳጃ ክፍሉ 1.50 ሜትር በ 1.50 ሜትር ስፋት ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፤

ለ) የመጸዳጃ ክፍሉ የተጣራ የበር ስፋት ከ0.90 ሜትር ማነስ የሌለበት ሆኖ ወደ ውጭ ተካፋች መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) በመጸዳጃ ክፍል ውስጥ በሦስቱም ጎኖች የእጅ መደገፊያ ያለው ሆኖ መደገፊያው ከግድግዳው ከ0.08 ሜትር እስከ 0.10 ሜትር ርቆ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

መ) የመጸዳጃ ክፍሉ መቀመጫ ከ0.57 ሜትር እስከ 0.60 ሜትር ከወለል በላይ ከፍታ ሊኖረው ይገባል፤

ሠ) የእጅ መታጠቢያ፣ ማድረቂያ፣ እና የሳሙና ማስቀመጫ የመጸዳጃ ክፍሉ ውስጥ የሚገጠም ሆኖ ከወለል በላይ ከ0.50 ሜትር እስከ 0.70 ሜትር ከፍታ ላይ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

ረ) ለአካል ጉዳተኞች ታስቦ የሚሰራው መጸዳጃ ክፍል ከውስጥ በሦስቱም ጎኖች የእጅ መደገፊያ ያለው ሆኖ መደገፊያው ከግድግዳው ከ0.08 ሜትር እስከ 0.10 ሜትር ርቆ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

ሰ) አንድ የጋራ መጸዳጃ ቤት ካሉት መጸዳጃ ክፍሎች ውስጥ አንደኛው አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ በማድረግ ባለ መቀመጫ መሆን ያለበት ሲሆን ሌሎቹ በተጠቃሚው ፍላጎት (ባለ ሳህን/ተርኪሽ ወይም ባለመቀመጫ) የሚወሰን ይሆናል፤

### 8.4.3. በጋራ መፀዳጃ ቤቶች የገላ መታጠቢያ ክፍሎች /cubicles/ ስታንዳርድ

ከላይ በንዑስ አንቀፅ 5.4.6 ከፊደል "መ" - "ሽ" የተዘረዘሩት የህዝብ የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ስታንዳርዶች ለጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ክፍሎች በተመሳሳይ መተግበር አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሚከተሉት ስታንዳርዶች ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡-

ሀ) እያንዳንዱ የጋራ ገላ መታጠቢያ ክፍል ቢበዛ ለ4 አባወራ/እማወራ ብቻ ማገልገል አለበት፤

ለ) የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ስፋት ለአካል ጉዳተኞችም በሚመች መልክ 1.50 ሜትር በ 1.50 ሜትር መሆን ይገባዋል፤

ሐ) የገላ መታጠቢያ ክፍል በር የተጣራ ስፋት ከ0.90 ሜትር ማነስ የለበትም፤

መ) የገላ መታጠቢያ ክፍል በር ከውጭ ተንጠልጣይ ቁልፍ ሊኖረው ይገባል፤

ሠ) አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ በማድረግ የገላ መታጠቢያ ክፍሉ ውስጥ በሦስቱም ጎኖች የእጅ መደገፊያ ያለው ሆኖ መደገፊያው ከግድግዳው ከ0.08 ሜትር እስከ 0.10 ሜትር ርቆ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

### 8.4.4. በጋራ መፀዳጃ ቤቶች የእጅ መታጠቢያ ስታንዳርዶች

ከላይ በንዑስ አንቀፅ 5.4.5 በህዝብ መፀዳጃ ቤቶች የእጅ መታጠቢያ ከፊደል "ለ"- "ሸ" የተዘረዘሩት ስታንዳርዶች ለጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ክፍሎች የእጅ መታጠቢያዎች በተመሳሳይ መተግበር አለባቸው፡፡

ይህ ስታንዳርድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒ ካቢኔ ከፀደቀበት ከነሐሴ 20 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

______________________

መኩሪያ ኃይሌ ተክለማርያም

የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር

# ዕዝሎች

## ዕዝል አንድ፡-የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች መነሻ ዲዛይን- (schematic design)




ይህ በስእል ለመግለጽ የተሞከረው የህዝብ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት የዲዛይን ዝግጅቱ በቦታ አጠቃቀምና የጠቀሜታዎች የእርስ በእርስ ዝምድና (ግንኙነት) ላይ የተመረኮዘ መሆኑን፤ እንዲሁም የወደፊት የማስፋፊያ ቦታ በግንኙነቱ ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን ተገቢ አካባቢና ቦታ ጭምር ለማሳየት የተሞከረ ሲሆን በሚቀጥለው ስዕል ላይ ለማሳየት የተሞከረው ደግሞ ደረጃውን የጠበቀ የሕዝብ የመጸዳጃና መታጠቢያ ቤቶች ሕንጻ ፕላን ከተሞች በስታንዳርድነት እንዲጠቀሙበት አማራጭ ዲዛይን ሆኖ እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## ዕዝል ሁለት፡- የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤቶች ዲዛይን



**ዕዝል ሶስት፡- የጋራ መፀዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች መነሻ ዲዛይን-** (schematic design)



## የማጣቀሻ ሰነዶች

1. Code of practice on Environmental Health:Singapore (as revised Nov 2013)
2. Public Toilet Design Guidelines, Bribane City Council: Australia, December 2013.
3. Public Toilet Strategy, Morinington Peninsula Shire: Australia, February 2012.
4. Public Sanitation Design Guideline; Water Services trust fund: Kenya,July 2009
5. Strategic Asset Management, Assets Property & Facilities Management, Improving Public Access to better public toilets-stirling council's comfort partnership scheme (CPS): Scotland
6. የተሻሻለው የከተሞች ልማታዊ መልካም አስተዳደር ግንባታ ማዕቀፍና የማስፈፀሚያ ስልቶቹ፡- ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር (ሚያዝያ 2006 ዓ.ም.)
7. የህዝብ ጤና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 200/1992 ዓ/ም፣
8. የኢትዮጵያ ህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ/ም፣
9. ለአረንጓዴ ልማት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስትራቴጂ፡- ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስራክሽን ሚኒስቴር (ሐምሌ 2006 ዓ/ም)